የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16[th] Year No. 43
ADDIS ABABA 28[th] July 2010

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፹፭/፪ሺ፪
የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.... ገፅ ፭ሺ፫፻፹፩

## CONTENTS

Regulation No. 185/2010
Defense Construction Enterprise Establishment
Council of Ministers Regulation ..........Page 5381

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፭/፪ሺ፪

### የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀፅ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀፅ ፵፯ (፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ «የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፭/፪ሺ፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ (ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዝ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪) ኢንተርፕራይዙ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የኢንተርፕራይዙ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንተርፕራይዙ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፭. ዓላማ**

ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩) በዋነኛነት የመከላከያን ግንባታ ፍላጎት ለማሟላት ማንኛውንም የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራ መሥራት፤

### Council of Ministers Regulation No. 185/2010

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF DEFENSE CONSTRUCTION ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. *Short Title***

This Regulation may be cited as the "Defense Construction Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 185/2010".

**2. *Establishment***

1) The Defense Construction Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**3. *Supervising Authority***

The Ministry of National Defense shall be the supervising authority of the Enterprise.

**4. *Head Office***

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

**5. *Purposes***

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to engage in any construction activity mainly to satisfy the national defense construction needs;

፪) በተጓዳኝ በሀገሪቱ የሚከናወኑ የመንገድ፣ የግድብ፣ የመስኖ፣ የሕንፃና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችን መሥራት፤

፫) ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን መሥራት::

**፮. ካፒታል**

ለኢንተርፕራይዙ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፰፻ ሚሊዮን (ስምንት መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፪፻፸፮ ሚሊዮን ፬፻፴፰ ሺ ፯፻፳፬ (ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺ ሰባት መቶ ሃያ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል::

**፯. ኃላፊነት**

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም::

**፰. ኢንተርፕራይዙ የሚቆይበት ጊዜ**

ኢንተርፕራይዙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል::

**፱. የተሻረ ደንብ**

የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፰/፪ሺ እና የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፱/፪ሺ በዚህ ደንብ ተሽረዋል::

**፲. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፰/፪ሺ ተቋቁሞ የነበረው የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፱/፪ሺ ተቋቁሞ የነበረው የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንተርፕራይዙ ተላልፈዋል::

**፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

2) in parallel, to engage in the construction of roads, dams, irrigation infrastructures, buildings and other construction works in the country;

3) to engage in any other related activities necessary to the attainment of its purposes.

**6. *Capital***

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 800,000,000.00 (eight hundred million birr) of which Birr 276,438,724.00 (Two Hundred Seventy Six Million Four Hundred Thirty Eight Thousand Seven Hundred Twenty Four Birr) is paid up in cash and in kind.

**7. *Liability***

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

**8. *Duration***

The Enterprise is established for an indefinite duration.

**9. *Repeal***

The Ddefense Construction and Engineering Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No.148/2008 and the Kality Construction and Construction Materials Production Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 149/2008 are hereby repealed.

**10. *Transfer of Rights and Obligations***

The rights and obligations of the Defense Construction and Engineering Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 148/2008 and the rights and obligations of Kality Construction and Construction Materials Production Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 149/2008 are hereby transferred to the Enterprise.

**11. *Effective Date***

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 28th day of July, 2010.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA